# ወያኔዎች የዛሬን ብቻ እንጂ የትላንቱና የነገን ማስብ ስለማይችሉ፤ በደመነፍስ ከሚኖሩ ፍጡርች ወይም ግኝትዎች (beings) አይሻሉም

*ከታጠቅ መንጂ- 15 January 2015*

የሕይወትን ወይም የመኖርን ትርጉም የምናውቀው ሞት ስላለ ነው ፣የወጣትነትን ትርጉም የምናውቀወ እርጅና ስላለ ነው ፣ የጨለማን ትርጉም የምናውቀው መብራት ስላለ ነው ፣ የለሊትን ትርጉም የምናውቀው የቀን ፀሐይ ስላለ ነው ፣ ድሃን- ድሃ መሆኑን የምናውቀው ሃብታም ሰላለ ነው ፣ የሰነፍ ተማሪ ሰነፍና የሚታወቀው በቱጉህ ተማሪ ውጤት ነው ፣ ፉንጋን- ፉንጋ የሚያሰኛት ቆንጆዎች ስላሉ ነው ፣የሰነፍ ሠራተኛ ሠነፍና የሚታወቀው ታታሪ ሠራተኛ በመኖሩ ነው ወዘተርፈ ። የተፈጥሮ ሕግጋት (Dialects of Nature) በተሰኘው መጻሓፉ “ያለተቃራኒው የተፈጠረ ፣ የኖረና የሚኖር ነገረ የለም” እንዳለው ፍሬደሪክ ኤንጅልስ በተመሳሳይ - የማሰብ ጭንቅላት ወይም ችሎታ ያለው ፍጡር (ሰው) ባይኖር - በደመነፍስ ሰለሚኖሩት ፍጡሮች (ግኝትዎች) ምንነት ባልታወቀ ነበር። ሳይንሳዊ ትንተናው ለሥነፍጥረት ተመራማሪ ሊሂቃን - ለ (ዚዮሎ ጂስቶች ፣ ኢንቲሞሎጂስቶች ፣ ሚሚኮሎጂስቶች ፣ ኦርኒስቶሎጂስቶች ) ወዘተ.. ትቼ 'የደመነፍስ' (instinct) ይፉ ትርጉም ፡- በኢ ማሰብ ፣ በኢንቃት ፣ በኢማስተዋል ወይም 'በዳበሳ' - መንቀሳቀስ ፣ መጓዝ ፣ መኖር ማለት ነው።

በደመነስ የሚኖሩ ፍጡሮች ( ግኝትዎች) ሕይወት አጠረም ረዘመ - ሕልው የሆኑበትን አካባቢ የተፈጥሮ ሃብት - በመጠቀም ፣ በመበዝበዝ እና በመደምሰስ ተፈጥሮ የለገሳቸውን - የአልሞትባይ ተጋዳይ (existentialism) ጥበብ በመጠቀም ከደቂቃ ወደ ደቂቃ ፣ ከሰዓት ወደ ሰዓት ፣ ከዕለት ወደ ዕለት ወዘተ.. ሕይወታቸውን ለማቆየት ይፍጨረጨራሉ ፤ ስለሚዋለዱም ዘር ተክተው ያልፋሉ ፤ ነገር ግን - ማምረት ፣ መፍጠር ፣ የሩቅና የቅርብ ፣ የትላንቱና የነገን ማስብ አይችሉም ።

ከበርካታ የስው ዘር ተሰጦዎች ወይም ችሎታዎች አንዱ እለት ከእለት ከሚኖርበትን 'ዛሬን' አሻግሮ ወይም አርቆ የማሰብ ችሎታ ነው ። በግለሰብ፣ በቤተስብ ፣ በማሕበረሰብ እና በሰከኑ መሪዎች ደረጃ በየትኛውም ታሪካዊ ዘመን (chronological time) ይኑሩ - የየትኛውም አገር ዜጎዎች ወይም ሰዎች ስለሚኖሩበት ዘመን ፍላጎታቸውን በማሟላትና በማሰብ ብቻ አይኖሩም ። የሚኖሩት ከትላንቱና ከነገውን እነሱነት ጋር በተዛመደና በተሣሰረ ሕይወት ውስጥ ነው ።

ሰዎች በየደረሱበት ዛሬ እየኖሩ በሕይወት ላልኖሩበት ስለትላንቱ እነሱነት እና በሕይወት ለማይደርሱበት ስለነገን እነሱነት እያስቡና እየተጨነቁ ይኖራሉ ። ስለትላንቱ - አገራቸውን ፣ ታሪካቸው ን፣ ባህላቸውን ፣ ዕደገታቸውን ፣ ገድላቸውን ፣ እሴታቸውን ወዘተ..

ከደረሱበት የዛሬን እነሱነት እና ከማይደርሱበት - የነገን እነሱነት ጋር እያዛመዱና እያገናዘቡ ይኖራሉ ።

በደረሱበት ዛሬ ላይ ሆነው ከመቶዎች ወይም ከሺዎች ዘመናት በፊት ጀምሮ የነበሩትን ቀደምቶቻቸውን ያወረሷቸውን ሁለእንተናዊ - የማንነት እሴቶቻቸውና ቅርሳቸውን ከነገው ትውልድ ማንነት ጋር የተሳሰረና የተቆራኘ (intertwined or linked) መሆኑን ስለሚያውቁ ተንከባክበው ፣ አዳብሮና አበልጽገው ለነገው ትውልድ ለማስረከብ ይጥራሉ ።ኖሮ ኖሮ ወደ ግብዓተ መሬት መግባት ብቻ ሳይሆን ጥሩ ነገር ለነገው ትውልድ አውርሶ ማለፍ የሰው ልጅ ባህሪና ልማዳዊ ግዴታ መሆኑንም ያውቃሉ ።

ለምሳሌ- ቅድመ አያቶቻቸው ወይም አያቶቻቸውን በአደዋ ጦርነት ፤ አያቶቻቸው ወይም አባቶቻቸውን በማይጨው ወይም በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ጦርነት የተዋጉበትን - ውጅግራ ጠመንጃ ፣ ዝናር ፣ጋሻ ፣ ጦር ፣ጎራዴ ወዘተ..በእንክብካቤና በታላቅ ኩራት ይዘው የተቀመጡ በርካታ - የነኚያ ጀግኖዎች ቤተስዎች መኖራቸውን አልጠራጠርም ፤እኔም ከነዚያ ቤተሰብዎች አንዱ ነኝ ። ልጅ ከአባቱ፣አባት ከአያት የተረከቡትን - ቄየ ፣ እርስት ፣ ጥሩ ሥራ ፣ መልካም ስም ፣ የአካባቢ ወይም የብሔራዊ ገድል ማስረጃ ቅርሶች ለልጆቻው አስረክቦ ያልፋሉ ።

በዛሬ ላይ እየኖሩ ስለዛሬን ሕይወት ማሰብ ፣ በዛሬ ላይ እየኖሩ ስለ ትላንቱ ማንነት ማሰብ ፣ በዛሬ ላይ እየኖሩ ስለነገን ማንነት ወይም ትውልድ ማሰብ ወይም በአንድ የሕይወት ዘመን የሶስትዮሽ ሕይወት መኖር ክንውን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ- የነበረ ያለና የሚኖር ነው (the same as the three dimensions of time) ።

የዘመናችን 'ገዢዎቻችን ወያኔዎች' ግን በዛሬ ላይ እየኖሩ 'ስለዛሬን ሕይወታቸው ብቻ ነው የሚያስቡት' ፥ አምበሻ ፣ እንጀራ ፣ ዳቦ ፣ ሹሮና ጎመን ከመብላት ወደ - ጮማ ፣ ቡሩንዶ ፣ ክትፎና ዘምናዊ የአውሮፓ ምግብ መብላት ከተሸጋገሩ ከወሃና ከጠላ ወደ - ቢራ ፣ ውስኪ ፣ ኮኛክና ሻፓኝ መጠጣት ከተሸጋገሩ ከጭቃና ከሳር ቤት ወደ - ቪላ ቤት ከተሸጋገሩ ከወንዝና ከምንጭ ውሃ ከመታጠብ ወደ - የፈረንሳይ ሻፓኝና ሽቶ በተቀላቀለበ ገንዳ ወሃ መታጠብ ከተሸጋግሩ ከቱታ ፣ ከሚሊሺያ አልባሳት (ዩኒፎርም) ፣ ከባህላዊ ነጠላና ኩታ ወደ አውሮፓ ሥራሽ - ሸሚዝ ፣ ክራባትና ሱፍ መልብስ ከተሸ ጋገሩ ከአገር ሠራሽ ጫማና ሰንደልዎች ወደ- አውሮፓ ሥራሽ መጫሚያዎች ከተሸጋገሩበእግር ፣ በአህያና በበቅሎ ከመሄድ ወደ- የድህረ ዘመናዊ የአውርፓ ምርት መኪና መንዳት ከተሸጋገሩ ከኬሻ ፣ ከቁርበትና ከንጨት አልጋ ወደ የአውረፓ - አልጋ ፣ ፍራሽና አንሶላ ከተሸጋገሩ ከቦርጭማና ካግዳሚ ወንበር (beanch) መቀመጫዎች ወደ አወሮፓ ሠራሽ - ምርጥ ሶፋዎችና ወንበሮች ከተሸጋገሩበባህላዊ ሰፌድና መሶብ አስቀምጦ በእጅ ከመብላት ወደ አውሮፓ ሠራሽ - ዘመናዊ ጠረጴዛዎች ፣ ሣህኖች ፣ ሹካዎች ፣ ማንኪያዎች ፣ ቢላዋዎች ወዘተ.. መብላት ከተሸጋገሩ ከባህላዊ - ውሃ ፣ ጠላ ፣ ቡና ወዘተ.. መጠጫዎች ወደ ወቅታዊ (latest) አውሮፓ ሠራሽ - የውሃ ፣ የቢራ ፣ የውስኪ ፣ የሻፓኝ

ብርጭቀዎችና ሲኒዎች ከተሸጋገሩ ከጠላና ከጠጅ ወይም ከመንደር መጠጥ ቤቶችና ሆቴሎች ወደ - ሻራተን ፣ ሂልተን ፣ ማሪዮት ፣ ሃራምቢ ፣ ግሎባል ወዘተ.. ሆቴሎች ሄደው -መብላት ፣ መጠጣት ፣ መደነስ ፣ ውለው ማደር ከተሸጋገሩልጆቻቸው ወደ - አሜሪካ ፣ አውሮፓ ፣ አውስትራሊያ ፣ ካናዳ ፣ ኒዩዝላንድ ፣ እስካንዳኔቪያ ወዘተ.. አገሮች ልኮ ማስተማር እስከ ቻሉ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር በባንክ ማስቀመጥ እስከቻሉ - በአጠቃላይ ቁሳቁሳዊ ፍላጎታቸውን (material want) እስከተሟላ ፡-

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን - ብሔራዊ ሉዓላዊነት ፣ ክብር ፣ታሪክ ፣ ባህል ፣ ተፋቅረውና ተሳሳሮ መኖር ፣ ስለትላንቱ እና ስለነገው ማንነታችን ወይም እኛነት ለእነሱ (ለወያኔዎች) ተረት ተረት ነው ፤ለምን ባፍጥማቸው አይደፋም ።የኢትዮጵያ -ዳርድንበር መደፈር፣መልካምድርዋ ተቀነጫጭቦ መሸጥ ፣ ጥንታዊ ቅርሶችዋና ተቋሞቿ መፈራረስ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሃብ ፣ በእርዛት ፣ በበሽታ ወዘተ.. መጎሳቀል እና የገፍ ሞት - በወያኔዎች ኅሊና ቦታ የለውም።

ሌላው ቀርቶ እኛ የኢትዮጵያ ጀግኖች ናቸው እያልን እነሱ ግን ትግራዊ ላልሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኑም አይደሉም የሚሉን 'አጼ የሓንስና ራስ አሉላ' እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ከባዕድ ወራሪዎች የተፋለሙለትን 'ምጽዋን' ከሻቢያ ጎን ተዋግተው ለኤርትራ አስረክበዋል ።

ለአጼ የሓኒስ 'የሚሰጥ የንግሥት ቪክቶሪያ {VICTORIA} መልእክት ይዞ ወደ አቢሲኒያ የተጓዘው {ጀራልድ ፖርታል} እ.አ.አ 1892 ዓ.ም (ወደ አቢሲኒያ ልዑክነቱ) በተሰኘው መጻሓፉ -ስለይዞት የሂደውን መልዕክት፣ስለአጼ የሓኒስና ስለራስ አሉላ እንደሚከተለው ጽፎዋል።

አጼ ዮሓኒስ በጣሊያኖች ተይዞ የነበረውን የጠረፍ ከተማ 'ጊሂንዳን' ወስደው -በምትኩ 'ሣሃቲ' በመባል ይጠራ የነበረውን የቀይ ባህር ጠረፍ መሬት ለጣሊያን እንዲሰጡ የሚያዝ መልዕክት ስለነበረ ፤ አጼ የሓኒስ እንኳንስ መሬት ሰጥተው ሊታረቁ እንደዚያ መታሰቡን አስቆጥቷቸው "ጣሊያኖቹም ሆኑ ሌሎች ባእዳን 'ምጽዋን' ይዞ የመቆየት መብት የላቸውም ።ምጽዋና ሁሉንም የደቡብ ምዕራቡ የቀይ ባህር ዳርቻዎች ለእኛነታቸው ታሪካዊ መብታችን ነው ። 'ከኢትዮጵያ መልካዓ ምድር መሬት ቆርሶ ወይም ሸርፎ የመስጠት ዝንባሌም፣ መብትም፣ ሥልጣንም' የለኝም' ።

ቱርኮች በጦር መሣርያ በልጠውን በመገኘታቸው ከ16ኛውን መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንዲወጣ ቢደረግም ያንን የተነጠቀውን መብታችን ለማስመለስ ከመጣር ኢትዮጵያ የተቆጠበበት ጊዜ ጭራሽ የለም።ምጽዋ በጣሊያኖች ሲወሰድ ቆሜ በዝምታ እንድመለከት ተጠየቅኩ ፤ ግብጾዎች ሲለቁ ምጽዋ ወደ ጥንትና ባለመብት ወደ ሆነው ሕዝቡ ይመለሳል" ማለታቸውን {ጀራልድ| ጻፍ።

ሉዑኩ የራስ አሉላን አነጋገር ከአጼ የሓኒስን አነጋገር የከረረና ድፍረት የተሞላበት እንድነበረ ሲገልጽ፥ "ጣሊያኖች በደጓሌ ድባቅ መታኋቸው ፤መልሼ እመታቸዋለሁ፤እኔ

የማውቀው የኢትዮጵያ የተፈጥሮ በር ቀይባህር መሆኑን ነው።ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ መሬት ማግኘት የሚችሉት እኔ የሮም ገዢ ከሆንኩ ብቻ ነው" ብለዋል በማለት{ጀራልድ} መሰከረ ።

ይህ አባባል ፣ይህ ጽንሰ ሃሳብ ፣ ይህ የፍጹም ጀግንነት መልዕክት ፣ይህ የፍጹም የአገር ፍቅር መተክል - ለዛሬዎቹ ወያኔዎች ትርጉም ይሰጥ ይሆን ? የአምሮ ሕዋሳቸውን ይነካ ይሆን ? አንብበውና ሰምተው ይርዱት ይሆን ? አይመስለኝ! አይመስለኝም! ምክንያቱም የዚህ ዓይነት ችሎታ ቢኖራቸውማ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ - ለዚህ ውድቀትና ቀውስ ባላበቁት ነበር ። በደመነፍስ የሚኖሩ ፍጡሮች (ግኝትዎች) ሕልው የሆኑበትን አካባቢ በመበዝበዝና በመደምሰስ እንደሚኖሩ ሁሉ ወያኔዎችም ኢትዮጵያን - በመበዝበዝ ፣ሸንሽኖ በመሸጥና በመደምሰስ 'ለዛሬ ቅንጡታቸውን ብቻ ስለሚኖሩ በደመነፍስ ወይም በዳበሳ ከሚኖሩት ፍጡሮች አይሻሉም ።

*ከታጠቅ መንጂ*

***16 December 2013***